# በDezember 10/2015 በNetzwerks konkrete Solidarität የተጠራ ሰላማዊ ሰልፍ

የጀርመን መንግስት ምንም እንኳን ስደተኞችን በሙሉ ፈቃደኝነት የሚቀበል መሆኑን „ከልብ ቢገልጽና ለአለም ቢያሳውቅም“ (Merkel) ዳሩ ግን በተለያዩ የሐገሪቱ ክፍል የስደተኞች መጠለያ እየተቃጠሉና ስደተኞ እየተሰቃዩ ይገኛሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አስተዳድሩ ከዚህ በፊት ያልነበረና „ስደተኛውን ለመመለስ የሚያስችል ጠንካራ ህግ እያወጣ ነው“(Seehofer)፡፡ ከዚህም ሌላ በአሁኑ ወቅት የስደተኞች ኑሮ ከከተማ ወጣ ባለ ስፍራና ከህብረተ-ሰብ መገናኘት በማይችሉበት ቦታ የተገደበ በመሆኑ ስደተኛውን የበለጠ የተገለለ ሊያደርገው ችሏል፡፡ ይህም ሁኔታ በአጭር ግዜ ውስጥ ይስተካከላል ብሎ መገመት አይቻልም፡፡

በዚህም ምክንያት ይህንን በመቃወም በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ቀን ተገኝተን አቋማችንን ለመግለፅ እንፈልጋለን:: ማንኛውም ሰው የቀለም፣ የፆታ፣ የሃይማኖትና ሌሎችም ልዩነቶች ሳያግዱት በፈቀደው ስፍራ ለመኖር እንዲችል አቋማችን ነው፡፡

በተጨማሪም ያልተዘጋ ድንበር፣ ለአደጋ ያልተጋለጠ መንገድ፣ ለሁሉም ነፃ ትምህርትና የጤና ዋስትና(ኢንሹራንስ) እንዲኖር እንጠይቃለን፡፡ ይህንንም በተመለከተ ለDezember 10/2015 ከቀኑ 17:00 ሰዓት ጀምሮ በፍራንክፈርት ሰላማዊ ሰልፍ የሚደረግ ሲሆን መነሻው ዋናው ባቡር ጣቢያ (Hauptbahnhof) ካይዘርዛክ (Kaisersack) ይሆናል፡፡

ይህንን ሰላማዊ ሰልፍ ጠንካራ ለማድረግ ቀደም ብላችሁ ድጋፋችሁን በድህረ ገፃችን http//nksnet.wordpress.com ላይ እንድታሳውቁን እየጠየቅን፡፡

የኢሜል አድራሻችንን:- teachers-ffm@nksnet.org በመጠቀም Aufruf 10 Dezember 2015 ብላችሁ ኢሜል በመላክ ስማችሁን እንድታስመዘግቡ እየጠየቅን ይህንንም ጥሪ በተለያዩ ቋንቋዎች ተፅፎ በድህረ ገፃችን ላይ ስለምታገኙት ለምታውቁት ሁሉ እንድታስተላልፉልን አደራ እንላለን፡፡

ግፊት ለድንበር ዘለል ነፃ አመለካከት

አንድነታችንን እናሳይ!!!

በእናንተ ትብብር das Netzwerk Konkrete Solidarität ይገነባል!!!